# <u>የኢትዮ - ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በእንግሊዝ ሀገር፣</u>
# <u>የአቋም መግለጫ፣</u>

በእንግሊዝ ሀገር የምንገኝ በርካታ ኢተዮጵያዊያን June 29 / 2008 ዓ.ም የወያኔ መንግስት የሀገራችንን የድንበር ቦታዎች ቆርሶ ለሱዳን ለመስጠት በሥውር የተፈራረመውን የክህደት ውል በሚመልከት፣ በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አዳራሽ ተሰብስበን ሰፊ ውይይት ከአካሄድን በኋላ ከዚህ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥተናል፡-

1. የሀገር ልዑላዊነትና የሕዝብ ደህንነት መጠበቅ የአንድ መንግስት ዋንኛ ተግባራት ሲሆኑ፣ ይህንን ማድረግ የተሳነው የወያኔ መንግስት የሀገሪቱን የድንበር ቦታዎች ለሱዳን ቆርሶ ለመስጠት የተፈራረመውን የሀገር ክህደት ውል አጥብቀን እንቃወማለን።

2. ይህን አሳፋሪ የክህደት ውል ተከትሎ፣ ከየቀያቸው ተፍናቅለው በባእድ ሀገር በእስር የሚንገላቱ ኢትዮጵያዊያን፣ በአስችኳይ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ አጥብቀን እየጠየቅን፣ በእስር ላይ ለሚደርስባቸው ጉዳት ሁሉ ተጠያቂው አሳሪው የሱዳን መንግስት ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን አሳፋሪ ውል የፈረመው የወያኔ መንግስትም እንደሆነ አጥብቀን ለማሳሰብ እንወዳለን።

3. በሀገርም ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን፣ በተለይ የታሪክና የህግ ባለሞያዎች፣ ይህ አሳፋሪ ውል በሀገር ላይ የተፈጸመ የክህደት ወንጀል መሆኑን፣ ለአለም በማሳወቅ፣ የበኩላችሁን የዜግነት ድርሻ እድትወጡ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

4. በእንግሊዝ ሀገር የምትገኙ ኢትዮጵያዊያን ይህንን የክህደት ውል በመቃወም ለአለም ተቋማት የተዘጋጀው የተቃውሞ ማመልከቻ ላይ በመፈረም፣ ድጋፋችሁን እድትገልጹና ሀገራቸውንና ቄያቸውን ለባእድ ሀገር አሳልፎ ላለመስጠት ከወያኔና ከሱዳን ጦር ጋራ በመጋፈጥ፣ በየቀኑ መስእዋትነት በመክፍል ላይ ለሚገኙ ንፁህን ዜጎች ተገቢውን ሁለገብ ድጋፍ እንድታደርጉ ጥሪ እናቀርባለን።

5. የተባበሩት መንግስታት፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታችሁ የአለም ተቋማት፣ ይህ ህገ ወጥ ውል የሚያስከትለውን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በማገናዘብ፣ ይህ አሳፋሪ ውል እንዲሰረዝ፣ አስፈላጊውን ጫና በኢትዮጵያና በሱዳን መንግስት ላይ እድታደርጉ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ሕገ ወጥ የክህደት ውል መቼም ቢሆን ተቀባይነት የለውም!!!**

**ልዑላዊነቷን የጠበቀች ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!**
**June 2008 ዓ.ም**
**ለንደን**